Institute of Development & Education for Africa, Inc.

webmaster@africanidea.org 1199 Whitney Ave Suite 523, Hamden, Ct USA

# ተኝቻለሁ እንጂ አልሞትኩም

## የእናት ኢትዮጵያ መልእክት ለኢትዮጵያ ሕዝብ

### ገላውዴዎስ ኣርኣያ ዶ/ር

**September 17, 2016** **መስከረም ፯ ፪ሺ፱ ዓ.ም.**

የዛሬ ሁለት ዓመት ከልዩ ልዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች የተውጣጡ ኢትዮጵያውያን ልጆቼ ሊጠዩቁኝ መጥተው ነበር፤ ወደ ነበርኩበት ገብተው ሲመለከቱኝ የአልጋ ቁራኛ መሆኔን ተገነዘቡና በዝቅተኛ አንደበት አንዳቸው ‘ወይኔ! እማማ ኢትዮጵያ ሞታለች እንዴ’ ሲል አዳመጥኩትና “ልጆቼ መጣችሁልኝ: በሉ ተቀመጡ: አይዟችሁ: ተኝቻለሁ እንጂ አልሞትኩም: ትንሽ አሞኝ ነው” አልኳቸው:: እነሱም ደስ አላቸው፤ ስለኔ ጉዳይና ስለ ዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች በሰፊው ከተወያየን በኋላ ለልማትና ለሰላም ትኩረት እንዲሰጠው ተስማማን፤ በተጨማሪም ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ባፋጣኝ የሚጎለምስበት መንገድ ለመቀየስ እና የመቻቻል ባህል መልህቅ እንዲጣል ማድረግ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሐላፊነት ሆኖ በተለይ ግን በዚሁ ረገድ ሐላፊነቱ መሸከም ያለበት መንግሰት መሆኑን ከተስማማን በኋላ ልጆቼ ወደየመጡበት ተመልሰው ለመሄድ ሲዘጋጁ “በርቱ: አንድ ሁኑ፤ ተባባሩ: እንዳትለያዩ: እንዳትነጣጠሉ፤ የውጭና የውስጥ ጠላቶች በሂይወታችሁ ሊዶሉቱ ነውና ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጉ፤ ምኞታቹሁና ፍላጎታችሁ ይሳካላችሁ ዘንድ የዘወትር ጸሎቴን አላቋርጥርም: ተባረኩ” በማለት ተሰናበትኳቸው::

አሁንም ቢሆን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ልጆቼ ተመሳሳይ መልእክት ነው የማስተላልፈው፤ ታሪክን መሠረት በማድረግ ምክር ልለግስላችሁ እፈልጋለሁ::

ይህም የምልበት ምክንያት ደግሞ ያሁኑ ትውልድ ታሪኩን የዘነጋ ሰለመሰለኝ ነው፤ እንድያውም የኔን የእናቱን ስም ከመጥራት ይልቅ የጎጥና የጎሳ ልዕልና ማሞገስ: ከዛም አልፎ የጎሳ ጥላቻ መሰንዘር ስለጀመረ ነው:: ይህ አዲስ የዘቀጠ ፖለቲካ የኔን ባህርይ አያንፀባርቅም:: የትግራይ ሰዎች ቢሂል አላቸው: 'ኣዴኣ ገዲፋ ሓትንኣ ትናፍቕ'፤ ትርጉሙ 'እናቷን ትታ አክስቷን ትናፍቃታለች' ማለት ነው:: የቢሂሉ መልእክት ደግሞ "የሃገርን ጉዳይ ወደ ጎን ትቶ የጎሳ ወይም ጎጥ ነገር ማስቀደም" ማለት ነው:: ከሁሉ ያሳዘነኝ ግን አንዳንድ ከአብራኬ የወጡ ሊሂቃንና ምሁራን የወጣቱን ትውልድ አካሄድ ስሕተት መሆኑን እያወቁ ሆን ብለው ብሔር ከብሔር ፤ ጎሳ ከጎሳ በማናቆርና በማጋጨት ሊበጠብጡኝ: ሊያሳምሙኝ: ከቻሉም ሊገድሉኝ እየሞከሩ መሆናቸውን ስለተረዳሁና በዚሁ እኩይ ተግባራቸውም የጦፈ እንቅስቃሴ ማካሄዳቸው ነው:: ነገር ግን እነዚህ ለባዕዳን የተገዙ ኃይሎች ወድያና ወዲህ ቢራወጡና ቢንቀሳቀሱም እኔን በመጠኑ ለመጉዳት ካልሆነ በስተቀረ ለሞት ሊዳርጉኝ አይችሉም:: እኔ እንደሆነ ፍንክች አልልም: አልሰበርም: አልበተንም: አልሞትም:: እነዚህ እርጉማን አላወቁትም እንጂ እኔ ለሚቀጥሉት የኢትዮጵያ ትውልዶች በቀጣይነት ለመንከባከብና ለማስተናገድ ፈር ለማስያዝም ጭምር ሓላፊነት ስላለብኝ: የግዴታ ሁሉንም ችግር በመቋቋም እስከመጨረሻ እዘልቀዋለሁ:: አበው ያሉትን ትዝ ይላችሁ እንደሆነ "እግዚኦ ኩነኔከ ሃቦ ለንጉሥ፤ ወፅድቄከኒ ለወልደ ንጉሥ" ነውና እኔም እንደ ንጉሡ (ባሁኑ ግዜ የመንግሥት መሪ) ሸክሙና ኃላፊነቱ የኔ ነው፤ "ኩኔነዉን" (ሸክሙን) እቀበለዋለሁ:: በጣም ከፋ ከተባለ ደግሞ "ፅድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ" ማለቴ አይቀርም:: ነገር ግን በልጆቼ ስለምተማመን ይኸን ያህል ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አይደለም በማለት ደግሞ ራሴን አጽናናለሁ::

እነዚህ የባዕድ የጥፋት መላክተኞች ሌላ ያላወቁት ነገር ወይም የዘነጉት ነገር ቢኖር የውጭ አገር የታሪክ ሊቃውንት ሳይቀሩ እንኳ ስለኔ ጉዳይ የዘገቡት አለ:: አንድ ከነዚህ የግሪክ ተወላጅ ሆኖ በመጀመርያው ምዕተ ዓመት አመተ ዓለም በሲሲሊ የምትባል ደሴት ይኖር የነበረ ድዮዶረስ ሲስለስ የተባለ የታሪክ ሊቅ ነው:: ዲዮዶረስ ስለኔ እንዲህ የሚል ትንቢት ተነበየ:- "ኢትዮጵያን የሚተናኮሏት: ሊያጠፏትም የሚሞክሩ ብዙ ወራሪ ኃይሎች ቢኖሩም ቅሉ ከነሱ ግን አንድ እንኳ የሚሳካለት አይኖርም::" እናንት ለባዕድ መሳርያ የሆናችሁት ግለሰቦች ወይም ስብስቦች ከድዮዶረስ ተማሩ እላችኋለሁ:: አለዛ በጠራራ ፀሐይ ይመሽባችኃል፤ ትጠፋላችሁ::

በሌላ በኩል ግን ምን ጊዜም ብሩህ ተስፋ ይታየኛል፤ እልፍ አእላፍ ጀገኖች ወልጃለሁ:: ለኔ ለናታቸው ሲሉ በጦር ሜዳ የወደቁ እና የተሰዉ ቁጥራቸው ብዙ ነው:: በዚህም ረገድ እጅግ በጣም የታደልኩ ነኝ ማለት እችላለሁ፤ ሌሎች

አፍሪቃውያን እህቶቼ ያላገኙትን እኔ በብቸኝነት አግኝቼዋለሁ:: ዕድሜ ለጀግኞች ልጆቼ፤ ከአፍሪቃ አህጉር እኔ ብቻ ካአውሮጳ ቅኝ ግዛት በማምለጥ ነፃ ሆኜ ለመቀጠል በቅቻለሁ:: የነፃነት አርማ ተምሳሌት ስለሆንኩም ሁሉም አፍሪቃውያን በተስማሙበት መሠረት አዲስ አበባ የአፍሪቃ መዲና ሆናለች፤ በዚህም ላይ የሰው ዘር መገኛ ነኝ፤ ቡናም ከኔ ምድረ-ከርስ ነው የፈለቀው:: እንግሊዝኛ ተናጋሪ ፈረንጆች coffee ያሉትን Kaffa መሆን ነበረበት:: ጣልያኖች ግን ከኛው ቋንቋ ሳይርቁ caffe ብለውታል:: ይህ ሁሉ ልዩ አገር ያደርገኛል: እኮራበታለሁ::

ጀግኖች ልጆች ባልወልድና ባላፈራ ኖሮ ግን ጉድ እሆን ነበር፤ ግን ከጥንት ጀምሮ እናታችንን አናስደፍርም የሚሉ ልጆች ስለነበሩኝ: ይመስገኖ ለአምስት ሺ ዘመን (ሦስት ሺ ዘመን የሚለውን ስሕተት ነው) ተጉዢያለሁ፤ ይህ ግን ዝም ብሎ በተአምር የሆነ ነገር አይደለም:: በጥንቱ ጊዜ አግአዝያን (ነፃ አውጪዎች) ከውጭ ወራሪ ኃይሎች በመከላከል እንዳልደፈር፤ የሕዝቤ ባህል: ኃይማኖቶችና: እሴቶች እንዳይጠፉ ረድተውኛል:: የአግአዝያን የልጅ ልጆች እንደነ አፈላስ: ኤዛና: ካሌብ የመሳሰሉት የአክሱም ነገሥታት ደግሞ ድንበሬን ከማስጠበቅ ባሻገር ግዛቴን አስፍተዉት ነበር:: እንዳሁኑ አያድርገውና በነዚህ ነገሥታት ዘመን ከኑብያ እስከ ሱማሌ ጠረፍና እስከ የመን ነበር የኔ ግዛት:: በ ፪፻ ከክርስቶስ ልደት በኋላ አፈላስ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ ሒጃዝ የሚባል አከባቢ (አሁን ሱዑዲ ዓረብያ) በኔ ግዛት እንዲሆን አድርጎ ነበር፤ ስልሳ ዓመት ከአፈላስ በኃላ ደግሞ ኤዛና ኩሽ ወይም ኑብያ (አሁን ሰሜን ሱዳን) በኔ ሉዓላዊነት እንዲተዳደር አድርጎ ነበር፤ ካሌብም እንደዚሁ በመጀመርያው ስድስተኛው ዓመተ ምሕረት (፭፻፲ ገደማ) የቀይ ባሕር ደቡባዊ አካል አቋርጦ የመንን ከኔ ግዛት ጋር ቀላቅሎት ነበር:: እነዚህ ነገሥታት ግን ዓላማቸው ወይም ተልእኳቸው ዳር ድንበርን ማስፋት ብቻ ሳይሆን እናንተ አሁን መልካም አስተዳደር የምትሉት ፅንሰ-ሐሳብ (በግብር መተርጎም የተሳናችሁ) እነሱ ያፈለቁት እና የተገበሩት ነበር ማለት ይቻላል:: ለአብነት: አፈላስ ከንጉሥ እንዲብስ በኋላ ለምንዛሪና ለንግድ ልውውጥ ገንዘብ አሰርቶ ነበር፤ ሁለት ዓይነት ገንዘብ የነሀስ እና የብር ለሃገር ውስጥ ንግድ፤ ሦስተኛው የወርቅ ገንዘብ ደግሞ ለዓለም ንግድ ልውውጥና ምንዛሪ አገልግሎት እንዲውል አድርጎ ነበር:: በዛን ጊዜ እኔ ብቻ ነበር በአፍሪቃ ገንዘብ የነበረኝ:: የምኮራበት ታሪካዊ ክስተት ነበር::

ኤዛና ፍትሐኛ ነበር፤ በማወቅም ባለማወቅም ህዝቡን እንዳይገፋ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርግ ነበር፤ አንድ ቀን እንዲህ ብሎ ጸለየ:- “የሰማይ ጌታዬ ሆይ ግዛቴን አጠንክርልኝ...ሀዝቤን በመልካም አስተዳደርና በፍትሕ እገዛለሁ፤ አልጨቁናቸውም:: እነሱም ንጉሥ ላደረገኝ ለሰማዩ ጌታ ብዬ ያቋቋምኩትን ዙፋን ይጠብቁ::”

ወንጌል ከኤዛና በፊት ነው ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰበከው፤ ክርስትና የተቀበሉም ነበሩ: የመጀመርያ ክርስትያን ንጉሥ ግን ኤዛና ነው፤ ስለሆነም ኤዛና ብሉይ ኪዳንን ክግሪክ ወደ ግእዝ እንዲተረጎም አደረገ:: ካሌብ ደግሞ የኤዛና ኮቴ ተከትሎ አዲስ ኪዳንን አስተረጎመ:: ካሌብ ግን ንጉሥ ብቻ ሳይሆን በፍልስፍና እና በሳይንስ የተካነም ስለነበር በቤቱ መንግሥቱ የተፈጥሮ ታሪክ ቤተመዘክር አሰርቶ ነበር፤ በ ቤተ መዘክሩም አንድ የታጨቀና የደረቀ አውራሪስ ተገኝቷል::

እነዚህ ነገሥታት የኔን የስልጣኔ ታሪካዊ ሂደት ፈር ስላስያዙት ለብዙ ሺ ዘመናት በተከታታይ የቁሳቁስና የአእምሮ ባህሎች ተከስተዋል፤ የእጅ ጥበብ: ሃዎልቶች: ልዩ ልዩ መሣርያዎች ቁሳቁሳዊ ባህል ሲያንፀባርቁ፤ ስነፅሁፍ: ፍልስፍና: ኃይማኖት: ቅኔ: መዝሙር: ዜማ ወዘተ ደግሞ የአእምሮ ወይም ስነልቦናዊ ባህል ነፀብራቆች ናቸው:: ይህም ስለሆነ ነው በዓለም ተደናቂነትን ያተረፉ ሐወልቶችና የውቅር ቤተክርስትያናት የተሰሩት፤ ማንኛውም ድምፅ መያዝ የሚችሉ የግእዝ ፊደላት የተፈጠሩት፤ ኢትዮጵያ የራሷ አውደ አዋርህ እንዲኖራት የሆነችው:: ይህ ስልጣኔ ታድያ እንደ ያሬድ እና ዘርአ ያቆብ የመሳሰሉ ሊቃውንት ለማፍራቱ የሚያስደንቅ አይሆንም::

የኔን ስልጣኔ በስነፅሑፍ: በታሪክ ተማራማሪዎችና እና በአድባራት ብራናዎች ተመዝግቧል:: ከዚህም በላይ የአክሱም ሃወልቶች፤ የላሊበላ የውቅር አብያተ ክርስትያናት እና የጎንደር የፋሲለደስ ግንቦች ምስክሮቼ ናቸው:: ቆየት ብለውም ሌሎች ልጆቼ ማለትም የሐረር ኢሚሮች ያሰሯቸው የግድግዳ ግንቦች፤ አባ ጅፋር በጅማ የተከለው ሥርወ መንግሥት፤ ጦና በወላይታ ያቋቋመው ጠንካራ መንግሥት፤ በሚቅሪጮ የተደገፈ የካፋ መንግሥት፤ የኦሮሞ ገዳ ዴሞክሬሲያዊ ሥርዓት ወዘተ የኔን ባህልና ሥልጣኔ በጥቅሉ የሚያንፀባርቁ እንጂ የዚህ: የዛ ብሔር ወይም ጎሳ ተብለው በጠባቡ የሚታዩ አይደሉም:: የድሮ ልጆቼም ይኸን ስለተገዘነቡ ባህላችንም ስልጣንያችንም የጋራ ነው በማለት መሃላ በመግባት ይኸንን እሴት ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላላፍ ነበረባቸው::

ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈውን ባህልና ሥልጣኔ ደግሞ ብዙ ቀናተኛና አርበኛ መሪዎችና ዜጎች ፈጥሯል:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በየጊዜው ፈተናዎች ደርሰውብኛል:: ለምሳሌ ከ ሺ፭፻፳ እስከ ሺ፭፻፵ ባለው ጊዜ አሕመድ ግራኝ ተፈታተነኝ፤ በጦርነት አውድማ ልጄን ልብነ ድንግልን ካሸነፈ በኋላ ደረቱን ነፍቶ እብሪት በተሞላበት ስነልቦና አብያተ ክርስትያናት አቃጠለ፤ የአብያተ ክርስትያናት የወርቅ መሳቅልትና አልባሳት ዘረፈ፤ ታሪካዊ ቅርሳቅርስና ንብረቶችን አወደመ:: ነገር ግን በልጆቼ

ብርታትና በበቁ አባቶች ጸሎት ከመዓቱ ተረፍኩኝ:: ልጄ ገላውዴዎስ ደግሞ በእናቱ በሰብለወንጌል እርዳታ ከነገሠ በኋላ ፖርቲጌዞች ስለደረሱለት ግራኝን አሸነፈ፤ የተቀሩትን የግራኝ የጥፋት ሠራዊት እስከ ሐረር አሳደዳቸውና የመጨረሻው ዕጣ ፋንታው ሐረር ግንብ አከባቢ በዕለተ ዓርብ ክርስቶስ በተሰቀለበት ቀን ተሰዋ:: በጣም አዘንኩኝ፤ ግን ስቅስቅ ብዬ አላለቀስኩም፤ የጀግንነቱ ኃይል ከዓይኔ ወስጥ እንባ እንዳይፈልቅና ከፊቴ ጠብ እንዳይል አደረገው:: በሕልሜ ደግሞ መላእክት የገላውዴዎስን ሬሣ ሲያነሱ አየሁኝ::

ሰባሦስት ዓመት ከገላውዴዎስ እልፈት በኋላ ልጆቼ ሱስንዮስና ፋሲለደስ በጎንደር ነገሡ፤ የጎንደር ሥርወ-መንግሥት ተጀመረ፤ ፋሲለደስ ራእይ የነበረው ስመጥሩ ንጉሥ ነበር:: በፋሲል ጊዜና በሌሎች ተከትለው የነገሡ እንደ እያሱና ባካፋ የመሳሰሉት ነገሥታት ጊዜ ጎንደር የአክሱም ወራሽና የኢትዮጵያ የባህል ሥልጣኔ መናኸረያ፤ የቁሳቁስና የአእምሮ ባህሎች መዲና ሆነች:: ከ ፱፯ ዓመት በኋላ ግን ሌላ ትልቅ ፈተና ደረሰብኝ፤ ግዛቴ በመሳፍንት ክፍለ-ሃገራት ተከፋፈለች:: ነገር ግን ምንም እንኳ በዚሁ ዘመን አንድነቴ ተዳክሞ ሕዝቤ ቢሰበጣጠርም፤ ሥልጣኑ የተኮላሸውን ንጉሥ ግን አሁንም ቢሆን የአንድነት ተምሳሌት ሆኖ ቀጠለ::

ታድያ፤ ጀግንነት ይወረሳል እንደሚሉት: ዘመነ መሳፍንትን የሚያከትም ኃይል ተነሳ፤ አንድነቴን የመለሰልኝ ጀግና ተፈጠረ: ስሙም ቴዎድሮስ ይባላል:: ሰሜን ኢትዮጵያን አንድ ካደረገ በኋላ ወደ ወለጋ ዘልቆ ነበር፤ ግን ዘመቻው ስኬታማ አልሆነም:: ቴዎድሮስ አስራ ሦስት ዓመት ከነገሰ በኋላ ሌላ ፈተና መጣብኝ፤ እንግሊዞች ቴዎድሮስን ለመውጋት መጡ: ብዙ ጠመንጃና መድፍ ይዘው ነበር የመጡትና ከቴዎድሮስ ጎን የተሰለፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት የእንግሊዝን ሠራዊት በብቃት መውጋት አልቻለም፤ እንደ ገብርዬ የመሳሰሉት ጀግኖች ደግሞ ተሰዉ፤ ቴዎድሮስ ሁኔታውን ካየ በኋላ ለእንግሊዝ እጄን አልሰጥም ብሎ ራሱን መስዋእት አደረገ:: ጀግናው ልጄ በመቅደላ ወደቀ፤ ጥልቅ ሐዘን ተሰማኝ፤ ለገላውዴዎስ ያየሁት ሕልም አሁንም ደግሜ አየሁት:: ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት በመመለስና ሕዝቡን በማስተባበር የተጫወተው ሚና በታሪክ ለዘልዓለም ህያው ሆኖ እንዲኖር አድርጎታል:: ከዚህ ባሻገር ግን ቴዎድሮስ አገሩን በስልጣኔ ለማራመድ ብዙ ዓበይት ነገሮችን አከናውኗል፤ ራእይ ስለነበረው መሬት ለሕዝቡ ለማከፋፈል ሙኩሯል፤ ቤተ መፃሕፍት አሰርቷል፤ ደሞዝ ያለው የሞያ ሠራዊት እንዲቋቋም ያደረገው ደግሞ እሱ ነው:: በተጨማሪም የአውሮጳ የኢንዱስትሪ ስልጣኔ አስመልክቶ መረጃ አግኝቶ ስለነበር አገሩ በዛው አቅጣጫ እንድትጓዝ ምኞት ስለነበረው መርከብ: መድፍ ወዘተ እንዲሰሩ ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር:: ታድያ ምን ዋጋ አለው! ያለ ጊዜው ተቀጨ::

ከቴዎድሮስ በኋላ ዮሐንስ አራተኛ ነገሠ፤ የቴዎድሮስን ኮቴ ተከትሎ ኢትዮጵያን አስተባበረ፤ ግዛቴንም አሰፋው፤ እስከ ጅማ ድረሰ:: ዮሐንስም ራእይ ስለነበረው እንዳሁኑ የፌደራል መዋቅር ባይሆንም የክፍለ-ሃገር ራስ ገዞች ስለፈጠረ በሸዋ ምንልክን አነገሰ፤ ተክለሃይማኖት የጎጃም ንጉሥ እንዲሆን ሾመው፤ በወሎ የራሱን ልጅ ኣርኣያሥላሴን አስተዳዳሪ አድርጎ ቢሾሞውም የወሎ ባላባት የሆኑትን መሐመድ ዓሊን ሚካእኤል ብሎ በማጥመቅና የራስ መዓርግ በመስጠት በእንደራሴነት እንድያገለግል አደረገ:: በጅማ ደግሞ አባ ጅፋር ለማእከላዊ መንግሥት እስከገበረ ድረስ የራስ አአዛዝ ነፃነት እንዲኖሮው አደረገ::

ዮሐንስ መልካም አስተዳድርን አስመልክቶ የጥንቶቹ ነገሥታት የነኤዛና ፍትሐዊነት ስለተከተለ ሕዝቡን በፍትሕ ነበር ያስተዳደረው:: ሃገሩን ወደፊት ለማራመድ ደግሞ የመጀመርያው ጤና ጥበቃ ጣብያ (clinic) እና የእህል ወፍጮ መሳርያ በንግሥነቱ ጊዜ ነው የተቛቛሙት:: ለሕዝቡ ኣርኣያ ይሆን ዘንድ ደግሞ በዋና ከተማው በመቐለ: ባደባባይ የመጀመርያ ክትባት ወሰደ:: ከሁሉም በላይ ግን ዮሐንስ ለሃገሩ ሉዓላዊነትና የድንበር ክብር ለማስጠበቅ ቀናኢ ስለነበር  በኔ ላይ የተነሱትን ጠላቶች ሁሉ መከታቸው፤ በጉራዕ እና ጉንዳጉንዴ ግብፆችን ሁለት ጊዜ አሸነፋቸው፤ ጣልያኖችም ሁለት ጊዜ በምፅዋዕ አከባቢ በሰሐቲና እና በዶግዓሊ አሸነፋቸው፤ በነዚህ ሁሉ ጦርነቶች የማይበገረው ጀግና የጦር መሪ አሉላ አባ ነጋ ነበር፤ እሱ በመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት ደግሞ ኩፊት ላይ በድርቡሾች ላይ ድል ተቀዳጀ:: ድርቡሾች ግን እንደገና በምዕራብ በኩል ሰርጎ በመግባት ጎንደርን አቃጠሉ ሕዝቤንም ፈጁት፤ ዮሐንስ በጣም ተቆጣ፤ በመጨረሻም ዮሐንስ ራሱ ባስተባበረውና በመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ መተማ አመራ፤ አራት ወር ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ግን ዮሐንስ ብልህ ስለነበር ለድርቡሾች መሪ ለ አቡ አንጃ የዕርቅ ደብዳቤ ፃፈለት፤ የደብዳቤው ይዘት ባጭሩ እንዲህ ይላል:- "አሁን እኔ ወደ አገርህ በመዝለቅ ደሀዉን ሕዝብ ብገድል፤ አንተም ወደ ሃገሬ ገብተህ ድሃውና ደካማውን በትገድል ምን ፋይዳ ይኖረዋል? ይልቁንስ በጋራ ጠላቶቻችን በአውሮጳውያን ላይ አንድነት እንፍጠር፤ እነሱ እኔን ከወረሩኝ አንተም አትተርፍም::" አቡ አንጃ ግን አሻፈረኝ አለ፤ ዮሐንስ ከድርቡሾች ጋር ጦርነት ይገጥምና ጦር ሜዳው ላይ ይሰዋል፤ ጀግናው ዮሐንስ መተማ ላይ ወደቀ:: ጥልቅ ሐዘን ተሰማኝ፤ ለገላውዴዎስና ለቴዎድሮስ ያየሁትን ሕልም እንደገና አየሁት::

ዮሐንስ ከወደቀ ከሁለት ወር በኋላ ምንሊክ ነገሠ:: በምንሊክ ዘመነ-መንግሥት በዮሐንስ ጊዜ የተጀመረውን የአውሮጳ የቅኝ ግዛት ፖሊሲ በተጠናከረ መልኩ

ሰለተተገበረ አፍሪቃን ጠቅላላ ወረሩት፤ ምንሊክም የግዴታ የኔን ግዛት ማስፋት ነበረበት:: ነገር ግን በምንሊክ ጊዜ ነው ደቡብ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ግዛት የሆነው የሚለውን አስተሳሰብ የተሳሳተ ነው:: የጥንቱ የአክሱም የቆዳ ስፋት ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ከኑብያ እስከ ሱማልያ ጠረፍ እንዲሁም ቀይ ባሕር ተሻግሮ እስከ የመን ነበር:: በዛጔ ዘመነ መንግሥት የሥርወ-መንግሥቱ ባልስልጣናት ሐረር ድረስ ተንቀሳቅሰውና ደርሰው ነበር:: በሱስንዮስ ጊዜም ወላይታና የአከባብው መለስተኛ ሃገረ-ግዛቶች ለማእከላይ መንግሥት ይገብሩ ነበር::

ምንሊክ እንደ ዮሐንስና ቴዎድሮስ አገሩን በስልጣኔ ጎዳና መምራት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ እንዳትወረርና እንዳትረክስ ጥረት አድርጓል:: በሺ ፰፻፹፰ (1896) የኢትዮጵያ አርበኞች በማሰለፍና ሕዝቡን በማስተባበር ጣልያኖችን ሰለወጋቸውና ስላሸነፋቸው እኔ ነፃ እና ሉዓላዊ ሆኜ ለመቀጠል በቅቻያለሁ፤ በዚሁ ረገድም የጥቁር ሕዝብ የነፃት ጮራ ተምሳሌት ከመሆኔም በላይ በግዜው ነፃነታቸውን ላልተቀዳጁ የአፍሪቃ ሃገራት በጠበቃነት ቆሜያለሁ፤ ትግላቸውንም በተግባር ደግፌዋለሁ:: ምንሊክ ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማራመድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል:: በዘመነ-መንግሥቱ የፓስታ ግልጋሎት: ቴሌግራም: ተሌፎን: የባቡር ሐዲድ ዝርጋታ: ባሕር ዛፍ: ሲነማ: የመጀመርያ የሚንስትሮች ምክር ቤት: ዘመናዊ ትምህርት ቤት በተግባር ለሕዝቡ ግልጋሎት አበርክተዋል::

ከምንሊክ በኋላ ተፈሪ መኮንን ኃይለሥላሴ ሆኖ ነገሠ:: ከአርባ ዓመት በላይም ገዛ፤ እርሱም በበኩሉ አገሩን በዘመናዊ መንገድ ለማስተዳደር የመጀመርያ የጦር አካዳሚ: የመጀመርያ ሕገመንግሥት: የመጀመርያ ፓርላማ: የመጀመርያ የእርሻ ኮሌጅ ከመፍጠሩም በላይ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ አድርጓል:: ነገር ግን በትረ መንግሥቱ ለአምስት ዓመታት ያህል ተቋረጠ፤ ጣልያኖች የአድዋ ሽንፈታቸውን ለመበቀል እንደገና ልያጠቁኝ ከአርባ አመት በኋላ መጡ:: ሕዝቤን በቦምብና በማስታርድ ጋዝ ደበደቡት፤ በአዲስ አበባ ሕዝቡን በገፍ ጨፈጨፉት: አቡነ ጴጥሮስን ረሸኑብኝ: የደብረ ሊባኖስ ካህናትና መናኩስት በጅምላ ፈጁብኝ:: ከፍተኛ ብሶትና ሐዘን ላይ ወደቅኩ:: ነገር ግን ተስፋዬ የጠዋት ጤዛ ሆኖ አልቀረም፤ ጀግኖች ልጆቼ ለኔ ክብርና ለክብራቸው ተዋጉ፤ ከጣልያን ጋር ያበሩ ከዳተኞች ቢኖሩም ቅሉ አርበኞቹ እንደነ ስዮም መንገሻ በትግራይ፤ አዳነ መኮንን በጎንደር፤ ኃይለማርያም ማሞ በሸዋ፤ በላይ ዘለቀ በጎጃም፤ገረሱ ዱኪ (አባ በራ) በወሊሶ ወዘተ ለነፃኔቴ ብለው በሽምቅ ውግያ ጣልያንን አጋፈጡት::

ከአምስት ዓመት በኋላ ኃይለሥላሴ ከግዞት ተመለሰ፤ በትረ መንግሥቱንም እንደገና ጨበጠ:: ከተመለሰም በኋላ ብዙ ማሻሻያዎችን አደረገ: ግን ከረዥም የሥልጣን ጊዜ አንፃር ሲታይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድህነትና ከቸነፈር መውጣት አልቻለም:: ለብዙ አሰርት ዓመታት አንቀላፈሁ፤ ግን አልሞትኩም::

ከኃይለሥላሴ በኋላ ደርግ የሚባል ጭራቅ መጣ:: ሕዝቤን ጨፈጨፈ፤ ወጣቱን በቀይ ሽብር ጨረሰ፤ ፩፯ ዓመት የ **ደ**ብድብ **ር**ገጥ **ግ**ዛ መንግሥት በታሪኬ ተወዳዳሪ የሌለው ሐዘን አደረሰብኝ፤ እኔን መምራት: ማራመድ: በስር ነቀል ለውጥ ማሰልጠኝ ይችሉ የነበሩ ምሁራንና ሊቃውንት ጠፉብኝ፤ ጭራቁ በላብኝ:: እርግጥ ነው በደርግ ጊዜ አንድነቴ አልተናጋም ነበር፤ የልጆቼ ሰለባ መሆን ግን ለ ፩፯ ዓመት የአልጋ ቁራኛ አድርጎኛል:: ባልሞትም እጅግ በጣም አሞኝ ነበር:: በመጨረሻ የቴዎድሮስ ጽዋ እጠጣለሁ ያለውን መንግሥቱ ኃይለማርያም ፈረጠጠ፤ ወደ ዚምባብዌ አመራ:: ወያኔ/ኢሐአዲግ ተካው::

ባለፉት ፳ ዓመታት ኢሕአዲጎች ብዙ ለውጥ አምጥተዋል፤ አያሌ መንገዶች: የጤና ጣብያዎች: ግድቦች: የባቡር ሐዲድ መስመሮች : ሰፋፊ እርሻዎች: በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች እና ትምህርት ቤቶች እንዲሁም የሕዝብ መኖርያ ቤቶች አሰርተዋል:: ዲሞክራሲ ግን አልፈቀዱም፤ ስለሆነም በሕግ የተመዘገቡና እውቅና ያገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደፈለጉ መንቀሳቀስ አልቻሉም፤ ጋዜጠኞች አላስፈላጊ ታስረዋል: አገር ቤት ለቀው እንዲወጡ የተገደዱም አሉ:: የፓርላማ አባላት መቶ በመቶ ኢሕአዲግ ከመሆን ይልቅ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአገራዊ ሸንጎው ወንበር ተሰጥቷቸው ድምፃቸውን የሚያሰሙበት መድረክ መፈጠር ነበረበት:: ባጭሩ በዘመነ ኢሕአዲግ መልካም አስተዳደር በሰፊው መተግበር ነበረበት፤ ግን አልተደረገም:: የኢሕአዲግ አመራር ራሱ ያመነበት ጉዳይ ነው::

በጎንደርና በኦሮምያ አከባቢ የተከሰቱት የፖለቲካ እንቀስቃሴዎች የመልካም አስተዳደር ጉድለትና መንግሥት ከሕዝብ ጋር ያለው ቅራኔ በአግባቡ እና በወቅቱ ለመፍታት ያለመቻል ነፀብራቆች ናቸው:: ባንድ በኩል እንዲህ ዓይነት እንቅስቃሴዎች በጎ አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይችላል:- የተነስ ጥሪ ደወል ሊያስተጋቡ ይችላሉ፤ በሌላ በኩል ግን የጎጥ ፖለቲካ እና የብሔር ጥላቻ መንፈስ ስላንፀባረቁ የሕዝቡን አንድነት የሚሸረሽሩ ይሆናሉ::

ተቃውሞ መልካም ነው፤ ሕዝቡ ይነቃል: የመንግሥት አመራሮቹም ይነቃሉ፤ የሕብረተሰቡ ማሕበራዊ ጤንነትም ይበለፅጋል:: ነገር ግን በስመ ተቃውሞ ንብረት

ማውደም፤ ለሕዝብ ግልጋሎት የሚጠቅሙ እንደ አውቶቡስ: ወሃ ማከፋፈያ ተቋማት: የአበባ እርሻ ማውደም የእጅግ በጣም ያዘቀጠ ባሕረ-ሐሳብ ነፀብራቅ ነው:: ሆን ብሎ የትግራይ ተወላጆች ማሳደድና ማጥቃት በጠባብ ፖለቲካ መታወር ብቻ ሳይሆን ወደ እብደት ያዘነበለ እንቅስቃሴ ነው የሚሆነው፤ ምንም ፋይዳም አይኖረውም: ኢትዮጵያን ከመጉዳት በስተቀረ:: አሁን የትግራይ ልጆች ሰለባ ይሁኑ እንጂ ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ መልኩ የአማራ ብሔር ተወላጆች በሐረር : በወለጋ በሌሎች አከባቢዎች ጭምር ኩፉኛ ተጠቅተዋል፤ ያም የእብደት ፖለቲካ ተግባር ነበር:: እንዲህ ዓይነት ቅጥ ያጣ ፖለቲካ አደገኛ ከመሆኑም በላይ የኔም ህልውና በጥያቄ የሚያስገባ ይሆናል:: በርትዓዊነት ከመረመርነው ደግሞ ማንኛውም ገለሰብ ወይም ስብስብ አንድ ብሔርን ነጥሎ ከጠላ: ካንቋሸሸና ካጠቃ ኢትዮጵያን አጠቃ ማለት ነው::

## አሁን ምን ማድረግ ይሻላል?

ከነገር ይቅደም: መጀመርያ ሃገራዊ እርቅ መደረግ አለበት:: መንግሥት ይህንን ኃላፊነት ተሸክሞ ከህዝቡ የተውጣጡ ምሁራን ያሉበት አንድ ግብረ-ኃይል እንዲቋቋም በአዋጅ ማስታወቅ አለበት:: ብዝሃነትን የሚያንፀባርቅ ግብረ-ኃይል ከተቋቋመ በኋላ ሰፋ ያሉና ጥልቀት ያላቸው ዓበይት ጉዳዮችን ያካተተ ፕሮግራም ማውጣት አለበት:: የሚካተቱ ዓበይት ጉዳዮች ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ልያጠቃልሉ ይችላሉ:-

፩. በሕገመንግሥቱ የተደነገጉትን የዴሞክራሲ ነፃነቶች እንደ የመፃፍና የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፤ የመምረጥና የመመረጥ መብት ማረጋገጥ ወዘተ ባስቸኳይ በግብር መተርጎም:: ግብረ-ኃይሉ አተገባበሩን ለመከታተልና ለማስፈፀም ከመንግሥት ስልጣን መሰጠት አለበት:: የዴሞክራሲ ሥርዓት የሕዝቡን መብት በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት የዴሞክራሲ ተቋማት ከቀበሌ እስከ ብሔራዊ ሸንጎ (ፓርላማ) መቋቋም ይኖርባቸዋል::

፪. የሕገመንግሥቱ አንቀፅ ፫፱ እቅድ በቀና መንፈስ የተፀነሰሰ ቢሆንም እምቅ ኃይሉ (ባልተገመተ እና ባልታሰበ መንገድ) የጎጥ: የጎሳና የብሔር ንቃተ-ህሊና ብቻ የሚያጎለምስና የአገር አንድነትን የሚያላላ ብሎም የሚንድና የሚበትን ሊሆን ይችላል:: አሁን የተከሰተውን ጸረ ኢትዮጵያ ዝንባሌና ተግባር ከወዲሁ ለማስወገድ ታድያ ዓንቀጽ ፫፱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ የፓርላማው የሕዝብና የፈደሬሽን ምክር

ቤቶች እንዲወያዩበት መንግሥት መምርያ መስጠት አለበት:: ግብረ-ኃይሉ ደግሞ የመከታተልና ዘገባ የመረከብ ሥልጣን ከመንግሥት ማግኘት አለበት::

ዓንቀጽ ፫፱ ከናካቴው ከሕገመንግስቱ አውጥቶ በሌላ ዓንቀፅ መተካት ሳይሆን: አስተካክሎ ማቅረብ ማለት ነው፤ ይህ ማለት ደግሞ የብሔሮች "እስከ መገንጠል" የሚለውን መብት (መብት ከተባለ) ቆርጦ በማውጣትና የብሔሮቹ ወይም ክልሎቹ የራስ አገዛዝ ነፃነት ወይም ራስን ችሎ የመስተዳደር መብት ግን እንዲፀና ማድረግ ማለት ነው::

፫. ግብረ-ኃይሉ የሚመራውን ሃገራዊ ዕርቅን አስመልክቶ የውይይት መድረኮች እንዲኖሩ ማድረግና እና በነዚህ በተከታታይና በቀጣይነት የሚደረጉ ውይይቶች ምሁራን: የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች: የመንግሥት ተወካዮች: የኃይማኖት መሪዎች ያሉበት ቢሆን ይመረጣል:: መድረኩም ለምልዓተ ሕዝቡ፤ በተለይም ለወጣቱና ለተማሪው ክፍት መሆን አለበት:: በውይይቱ የሚቀርቡ ዓበይት ነጥቦች የሚከተሉትን የሚያካትቱ መሆን አለባቸው:-

**ሀ.** በሕዝብና በመንግሥት ያለውን ያለመግባባት ወይም ቅራኔ በሰላማዊ መንገድ እንዴት መፈታት እንዳለበት::

**ለ.** የአሁኑ የፖለቲካ ውጥረትና ያስከተለው ቀውስ በቅጡ ተጠንቶ መፍትሔ ማበጀት:: ለአብነት፤ የድንበር ወይም የማንነት ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት፤ ለምሳሌ የኦሮሞ ወጣቶች የአዲስ አበባ ልዩ ክልል እና የኦሮሞ ገበሬዎች መፈናቀል አስመልክቶ ያቀረቡትን ቅሬታና ስሞታ (እንደ ከስና ንዝንዝ ሳይታይ) በመድረኩ ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል:: በመድረኩ ለውይይት ሲቀርብ ብቻ ነው ሐቁን የሚታወቀው:: በአዲስ አበባ ልዩ ክልል ምክንያት ሊፈናቀል የሚችል የኦሮሞ ገበሬ ሊኖር ይችላል ወይ? መድረኩ ይመልሰዋል! ከረብሻው በፊት መንግሥት አስፈላጊውን እርምጃ ቢወስድ ኖሮ ሰላሙና እርጋታው ባልደፈረሰ ነበር::

በተመሳሳይ መልኩ በጎንደር የተከሰተው የሕዝብ እንቅስቃሴ ከመጀመርያውኑ ከሕዝብ በመወያየት ችግሩን መፍታት ይቻል ነበር:: የጎንደሩ የመጀመርያው "ሰላማዊ" ሰልፍ የተባለው ሰላማዊ እንዳልነበረ ግልጽ ነው፤ በመጠኑም ቢሆን ተቃዋሚ የሚባሉ ኃይሎች ጠመንጃ (ጠብ-መንጃ) በመጠቀም መለስተኛ ጦርነት አካሂደዋል:: ፖሊሶች ተገደሉ፤ ተራ ሰው ሞተ፤ የትግራይ ተወላጆች ንብረት ተቃጠለ:: ሁለተኛው የጎንደር የሕዝብ ተቃውሞ ግን በሰላማዊ ሰልፍ የተመራና

የተጠናቀቀ ነበር:: ሰልፈኞቹ የታሰሩትን ይፈቱልን: መሬታችን ይመለስልን ብለው ዘምረዋል፤ መብታቸው ነው፤ መንግሥት ደግሞ የልብ ትርታቸውን ማዳመጥ አለበት:: "መሬታችን ይመለስልን ሲሉ ወልቃይት ከትግራይ ወደ ጎንደር ይመለስ" ማለታቸው ነው መሰለኝ:: ግብረ-ኃይሉ "የወልቃይት ጉዳይ የድንበር ወይስ የማንነት ጥያቄ? በማለት ለመድረኩ ተሳታፊዎች ሃሳብ እንዲያፈልቁ መጋበዝ ይችላል:: የሚወስነውስ ማን ነው? ሰብስቦችና ልሂቃን ወይስ የወልቃይት ሕዝብ? የወልቃይት ሕዝብ ስለራሱ ጉዳይና ዕጣ ፈንታ የሚወስነው ራሱ ከሆነ ረፈረንደም ይካሄድና ይለይለት::

**ሐ.** የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክና የፖለቲካ ካርታዎች አስመልክቶ በምሁራን ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው መድረኩ ይወያይበት:: ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃ የቆየች አገር ብትሆንም ካርታዋ ግን ብዙ ጊዜ ተቀያይሯል:: በጣልያን የአምስት ዓመት ወረራ ጊዜ ከሞላ ጎደል በቋንቋ የተካለሉ ክፍላተ ሃገራት ተፈጥረው ነበር:: በኃይለሥላሴ ጊዜ የጣልያኑ ካርታ ተቀይሮ ጠቅላይ ግዛቶች ተፈጠሩ፤ የነዚህ ጠቅላይ ግዛቶች ቆዳ ስፋት ግን በየጊዜው ተቀያይረዋል:: ለምሳሌ የአርሲ ሰሜናዊ አካል ከሸዋ እንዲሆን ተደረገ፤ ሐረርጌን ለሁለት በመግመስ ባሌ የሚባል ክፍለ-ሃገር ተፈጠረና ኢትዮጵያ ከ ፲፪ ወደ ፲፫ ክፍላተ-ሃገራት ያላት አገር ሆና ተቀየረች:: ቆይቶም የፈደሬሽኑ ትስስር አብቅቶ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ተዋሃደችና ፲፬ ከፍላተ-ሃገራት እንደ ጠቅላይ ግዛቶች በዘውዱ ስር ተቆራኙ:: በደርግ ግዜም እንደዚሁ ራስ-ገዝ የሚባሉ ከፍላተ-ሃገራት ተፈጠሩና ኤርትራን ለሁለት በመግመስ ዓሰብ ወይም አፋር ራሱ የቻለ ራስ-ገዝ ሆነ:: አሁን ደግሞ በኢሕአዴግ ጊዜ ኢትዮጵያ በ፱ ክልሎች ተከፋፍላለች፤ በዚሁ የአከላል ሂደት ላይ ወልቃይት-ፀገደ ከትግራይ ጋር እንዲሆን ተደርጓል::

በኃይለሥላሴ እና በደርግ ጊዜ የኢትዮጵያ ካርታ ሲቀያየር በሕዝቡ ወይም ሊሂቃኑ ዘንድ ተቃውሞ አልተደረገም፤ የአርሲ ግዙፍ መሬት ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ሲጠቃለል ተቃውሞ ይሁን ትችት የቀረበ የለም፤ አንዳንድ የጂኦግራፍ ምሁራን ግን በዚሁ ጉዳይ ላይ ጽፈው ሊሆኑ ይችላሉ:: ታድያ የወልቃይት-ፀገደ ለምንድነው ይኽን ያህል ውዝግብና ረብሻ የፈጠረው? ይኽን አስመልክቶ ምሁራን ሰፊና ጥልቅ ጥናታዊ ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ግብረ-ኃይሉ ማበረታታት አለበት::

**በ**. በፖለቲካ ጠንቅና ውዝግብ ጊዜ ወይም በግርግር መሃል የምልአተ ሕዝቡ አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ይዘነጋል:: ባሁኑ ጊዜ ሕዝቡ (አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሃ ነው) በኑሮ ወድነትና በዋጋ ግሽበት እየተሰቃየ ነው ያለውና ግብረ-ኃይሉ ለዚሁ ችግር መፍትሔ ከመንግሥት መምጣት እንዳለበት ከመጠቆም ባሻገር ፖሊሲ-ነክ

ነገሮች እንደ የምርት አቅርቦት በሃሳብ ደረጃ ማቅረብ አለበት:: ለምሳሌ ኢትዮጵያ ለውጭ ምንዛሪ በማለት ለዓለም ገበያ ከምታቀርባቸው እንደ ቡና: ቆዳ: ሰሊጥ የመሳሰሉት ምርታ-ምርት በስተቀረ የሃገር ውስጥ ፍላጎት ማርካት የሚኖርባቸው እንደ ገብስ: ስንዴ: በቆሎ: እንቁላል: ደሮ: ከብት ወዘተ ወደ ውጭ መላክ የለባቸውም:: አለዛ ሕዝቡ የዋጋ ውድነት ሰለባ ሆኖ ለረዥም ጊዜ ይቀጥላል::

**ሰ.** መንግሥት ብዙ ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት የምሌኔም አጀንዳ በማስተጋባት "የኢትዮጵያ ዋና ጠላት ድህነት" ነው ብሏል፤ ሙሱና ደግሞ ስር የሰደደ ነቀርሳ መሆኑን በተደጋጋሚ ተናግሯል፤ ሙሱና እንደ ባህል ባንሰራራበት ጊዜ ድህነት ከምድረ ኢትዮጵያ ይጠፋል ማለት ግን ዘበት ነው፤ ሙሱናው በሰፊው ሕብረተሰብ በቻ ሳይሆን በከፍተኛ ባለስልጣናትም ጭምር እንደ ባህርያዊ ልምድ ስለተያዘ: የዓሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ ነውና ባፋጣኝ መፍትሔ ቢገኝለት ይመረጣል::

በመጨረሻም እኔ እናታችሁ አደራ የምላችሁ ነገር ቢኖር ወሬና አሉቧልታ አስወግዳችሁ የውጭ አገር ተላላኪ ስብስቦቹን ማጋለጥ እና አንድነታችሁ እንዳይሸረሸር በከፍተኛ ጥንቃቄ መዳዝ እንዳለባችሁ ነው:: ከፋፋይ ምስጥ ቡዱኖች በተለያየ መስክ በመግባት እየተንቀሳቀሱ ነው፤ ባህላችሁና ሃይማኖታችሁን ከበረዙና ካዳከሙ በዃላ የጋራ ማንነታችሁን (ኢትዮጵያውነትን) በቀላሉ ማውደም እንደሚችሉ መዘንጋት የለባችሁም:: ኢትዮጵያን ለማዳከምና ከተቻለም ለመበተን የሚሯሯጡ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ህሊና የላቸውም:: እነሱ እንደሆነ በተለያዩ የምዕራብ ሃገሮች ከተሞች በተመቻቸ ሁኔታ ነው የሚገኙት፤ ከሩቅ ሆነው እሳት የሚለቁ እሳቶች አሉና ተጠንቀቁ፤ እሳቱ ባገር ውስጥ ከተቀጣጠለ ደግሞ የሚቃጠሉት እነሱ ሳይሆን እናንተ ናችሁ:: ስለሆነም: እናንተ በጎሳ: በብሔር እና በኃይማኖት ሳትነጣጠሉ ከንዳችሁን በማስተባበር አሳፍሯቸው:: ሌላ ማላመጥ ያለባችሁ ነገር አለ:- ኢትዮጵያውያን የሚባሉ ከዳተኞች አገራቸውን ለማጥፋት ሲቍነጠነጡ የውጭ አገር ኃይላት በዚሁ ሴራ ወስጥ ሽርጉድ ቢሉ ምን ያስደንቃል?

በዚሁ ድርሳን (ደርሳነ-ኢትዮጵያ ማለት ትችላላቹ) የቀረበው መልእክት በሙሉ የኔ ነው፤ አቅራቢው ደግሞ የኔ ጸሐፊ ትእዛዝ ነው:: በርቱ: ሰላም ሁኑ: በቸር ይግጠመን::

**የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ) መብት በሕግ የተደነገገ ነው::**
**All Rights Reserved Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA) 2016**